


# ቀን አንድ፡- በመጀመሪያ እግዚአብሔር[ዘፍ1[1]]





ከሁሉም ቀድሞ ፤ ዘመናትም ከመጀመራቸዉ በፊት እግዚአብሔር አለ፡፡ የዓለማት ፈጣሪ እግዚአብሔር፤ መጀመሪያ የሌለው መጀመሪያ፥ መጨረሻም የሌለዉ መጨረሻ (አልፋና ዖሜጋ)፤ ሁሌም ያለ÷ ሁሌም ዘለላማዊ አሁን የሆነ፤ በራሱ የነበረ፥ ያለ፥ የሚኖርም አምላክ (ያህዌ) ነው፡፡





ስለዚህ ምንም መጀመሪያ ይሁን መጨረሻ የሌለውን፤ በራሱ የሚኖር አምላክን መጀመሪያ ማወቅ አይቻልምና፤ እንደ መጽሓፍ ቅዱሱ የመጀመሪያ ዓረፍተ-ነገር "እግዚአብሔር በመጀመሪያ" ብሎ ከመቀበል ውጭ ሌላ አማራጭ የለም!



† በዚህ የተነሳ ነዉ መጽሓፍ ቅዱሳችን ከሁሉ በፊት እግዚአብሔር እንዳለ ለድርድር እንኳ ሳያቀርብ፤ "በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ" ብሎ የጀመረዉ፡፡ እርሱ ከጥንትም ጀምሮ እኔ ነዉና!

በዚህም የዘፍ 1[1] መጀመሪያ ከፍጥረቱ በፊት የነበረውን መጀመሪያ የሚያመላክት እንደሆነ እንረዳለን፡፡

መሠረታዊ ጥቅሶች፤

- ኢሳ44[6-7] “የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር፥ የሚቤዠም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፥ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም። እንደ እኔ ያለ ማን ነው? ይነሣና ይጥራ ይናገርም፤ ከጥንት የፈጠርሁትን ሕዝብ ያዘጋጅልኝ፥ የሚመጣውም ነገር ሳይደርስ ይንገሩኝ።”
- ኢሳ48[12-13] “እኔ ነኝ እኔ ፊተኛው ነኝ እኔም ኋለኛው ነኝ። እጄም ምድርን መሠረታለች ቀኜም ሰማያትን ዘርግታለች በጠራኋቸው ጊዜ በአንድነት ይቆማሉ።”
- ኢሳ40[28-29]," እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ፥ የምድርም ዳርቻ ፈጣሪ ነው አይደክምም፥ አይታክትም፥ ማስተዋሉም አይመረመርም። ለደካማ ኃይልን ይሰጣል፥ ጕልበት ለሌለውም ብርታትን ይጨምራል።”
- ኢሳ44[24] “ሁሉን የፈጠርሁ፥ ሰማያትን ለብቻዬ የዘረጋሁ ምድርንም ያጸናሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ ከእኔ ጋር ማን ነበረ?”
- ኤር51[15]“ምድርን በኃይሉ የፈጠረ፥ ዓለሙን በጥበቡ የመሠረተ፥ ሰማያትንም በማስተዋሉ የዘረጋ እርሱ ነው።”



መሠረታዊ ጥቅሶች፤

- መዝ90[3] “ተራሮች ሳይወለዱ፥ ምድርም ዓለምም ሳይሠሩ፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ አንተ ነህ።”.........አይለወጥም!
- መዝ102[25-27]“አቤቱ፥ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፥ ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው። እነርሱ ይጠፋሉ፥ አንተ ግን ትኖራለህ ሁላቸው እንደ ልብስ ያረጃሉ፥ እንደ መጐናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ፥ ይለወጡማል አንተ ግን ያው አንተ ነህ፥ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም።”
- ሮሜ1[20] “የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና”
- ዕብ11[3] “ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ፥ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን።”
- ቆላ1[16] " የሚታዩትና የማይታዩትም፥ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፥ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው። ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል።”



እንግዲህ.....

በመጀመሪያ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሰማይንና ምድርን ፈጠረ፤ የሚለው የዕብራይስጡ 'ኤሎሂም' በነጠላ ግስ ብዙ ቁጥር ማሳየቱ፤ ሥላሴ በፍጥረት ሥርዓት በእኩል ተሳታፊ እንደነበሩ ያሳያል!



- ስለ አብና ወልድ [1ቆሮ8[5-6]]፤
- ስለ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ [ዘፍ1[2]፤ኢዮ33[4]፤ መዝ 104[30]]፡፡



# የሆነ ሆኖ የፍጥረት ስርዓቱ በዋናነት የተመራዉ በወልድ ነው፡፡

[ምሳ 8[22-31] ከ1ቆሮ1[24] ጋር ያነጻጽሩት ፣ ዕብ1[2]]

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጥረትን የፈጠረ ብቻ ሳይሆን አሁንም አጽንቶ የያዘዉ እርሱዉ ነዉ!

[ቆላ1[16] ]





" እስካሁን ያየነዉ በዚህ በዘፍ 1[1] ያለዉን መጀመሪያ፣ ከፍጥረቱ በፊት የነበረውን መጀመሪያ የሚያመላክት እንደሆነ ነበር፡፡"





" መጽሐፍ ቅዱሳችን ሌላ የመጀመሪያ ፅንሰ ሃሳብ እንዳለ በሀዲስ-ኪዳን መግቢያ ላይ ይገልጻል፡፡"



† ሌላኛው "መጀመሪያ" ዮሃንስ ወንጌላዊዉ የሚለው መጀመሪያ ነው፡፡ [ዮሃ1[1-5]] ይኸኛው መጀመሪያ 'ወልድ' በመለኮታዊ ክብሩ ከአብ ጋር ያለውን ዘላለማዊ አንድነቱን የሚገልጽ ነዉ፡፡

- በዚህም ይህ በእግዚአብሔር ዘንድ በመጀመሪያ የነበረው፥ እግዚአብሔር የሆነው፥ የእግዚአብሔር ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ሁሉ በርሱ የሆነ፥ ከሆነውም አንዳች እንኳ ያለርሱ የልሆነው አምላክ እንደሆነ ይገባናል፡፡



† ይህ በእግዚአብሔር ዘንድ በመጀመሪያ የነበረው ቃል፥ ይህ ፍጥረትን ያስገኘው ቃል፤ ሁሉ በእርሱ ሆኗልና፥ ከሆነውም አንዳች እንኳ ያለእርሱ አልሆነምና፤ በእርሱ ሕይወት ስለነበር፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን ስለሆነች፤ ቃል ሥጋ ሆኖ፥ ፀጋንና እውነትንም ተሞልቶ፣ በእኛ በማደር፣ ሕይወትን ሰጥቶናል፡፡ [ዮሃ1 1-14]





† ይኸዉ ወንጌላዊ ሐዋሪያ

ከመጀመሪያ የነበረው ዘላለማዊ አምላክ እግዚአብሔር፣ በስጋ እንደተገለጠ፤ በአብ ዘንድ ከመጀመሪያው የነበረው ሕይወት፣ ሰዉ እንደሆነ፤ እርሱም በአይኖቹ እንደየዉ፥ በእጆቹ እንደዳሰሰዉ፥ በጆሮቹም እንደሰማዉ፤ በዋለበት እየዋለ፥ ባደረበትም እያደረ ከእግሮቹ ሥር እንደተማረ በመልዕክቱ ገልጧል፡፡

[1ዮሃ1 1-4]





በዚህም የዘላለም ሕይወት፤ የታየው፥ የተዳሰሰው፥ የተሰማዉ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ፤ መገለጡም አዳም ቅጠል በልቶ ከእግዚአብሔር ጋር በመጣላቱ፣ በመሞቱም፤ በስሙ ለሚያምኑ ሁሉ ሕይወትን ለመስጠት እንደሆነ እናያለን፡፡ በርሱ ሕይወት ነበረች፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች። ይላልና፡፡



⁘ ሚስጢሩ”የዛሬ 2000 ዓመት የዘላለም ሕይወት በሥጋ ተገለጠ፣

“የምንነቃም ብንሆን፥ የምናንቀላፋም ብንሆን ከእርሱ ጋር አብረን በሕይወት እንኖር ዘንድ፣ ስለ እኛ ሞተ፡፡” [1ተሰ5 10]

መጽሓፍ ቅዱስም ስለተገለጠዉ ሕይወት እንዲህ ይላል፡

[ዮሃ6$^{47}$] “በእኔ የሚያምን፣ የዘላለም ሕይወት አለው።”

[ዮሃ6$^{49}$] “የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፡፡”

[ዮሃ10$^{10}$] “...እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ።”

[ዮሃ10$^{28}$] “እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘላለምም አይጠፉም፥ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም።”

[ዮሃ11$^{25}$] “እኔ ትንሣኤና ሕይወት ነኝ፡፡ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል።”



መጽሓፍ ቅዱስም ስለተገለጠዉ ሕይወት እንዲህ ይላል፡

[ዮሃ14$^{6}$] “ኢየሱስም፡- እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።”

[ዮሃ17$^{3}$] “እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።”

[ዮሃ20$^{31}$] “ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል።”



አንድም፣ የዘላለም ሕይወት በሰውም ይሁን በመላእክት ፀሎት የማይታደል፥ በመመጽወትም ይሁን በመፆም ዓይነት ስርዓት የማይመጣ ፥ አሊያም የሆነ ሀይማኖታዊ Process ሳይሆን፤ የዘላለም ሕይወት ራሱጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነና፤ የሚገኘዉም የድንግል ማሪያምን ልጅ ካለወንድ ዘር በድንግልና ተጸንሶ የተወለደዉ እርሱ የሰዉ ልጆች ሕይወት ነዉ። ብሎ በማመን ብቻ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡



እንግዲህ . . . . . . በመጀመሪያ እግዚአብሔር ከሚለዉ አስተምሮ መሰረተ ሃሳብ አኳያ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ማመን ወይም ክርስቶስን መቀበል ማለት በራሱ ምን ማለት ነዉ???

## መጀመሪያ የነበረው፥

ሰማይና ምድርንም የፈጠረው እግዚአብሔር፤
አዳም በመበደሉ የተነሳ የሰው ዘር ሁሉ
ስለሞተ፤ እርሱ ደግሞ የሰው ሕይወት ስለሆነ፤
ከንፅህት፥ ቅድስት፥ ድንግል ማርያም ያለወንድ
ዘር ተወልዶ፤ ፍጹሙ አምላክ፣ፍጹም ሰዉ
ሆኖ፥ በሥጋም ተገልጦ የተዳሰሰዉ፥ የታየውም
የዘላለም ሕይወት እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ፤
ከእርሱ ጋር በሕይወት እኖር ዘንድ ሞቶልኛል፥
እርሱ ሕይወቴም፥ ትንሣኤዬም ነው። ብሎ
ማመን ነው። "

እርሱም የሰጠን ተስፋ ይህ የዘላለም ሕይወት
ነውና። [1ዮሃ2[25]፤ዩሃ5[26]፤ራዕ20[15]]

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።